የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም

# ለአዲስ ኢትዮጵያዊ እሥራ-ምእተ-ዓመት (፫ኛ ሚለንየም)
## ራእያችን፥ ስጋታችንና ምኞታችን፤

የታሪክ ባለፀጋ የሆነችው አገራችን ኢትዮጵያ ከአኩሪና ስብጥርጥር ባህሎቿ ባሻገር በውስጥ በገዥዎች ትርምስና ከውጭ ጠላቶቿ በተደጋጋሚ በተሰነዘሩ የወረራ ሙከራዎች ስትደማ የቆየች አገር ናት፡፡ ሆኖም በዚህ በግጭቶች በተትረፈረፈ ታሪኳ ውስጥ የተገባደደው ሃያኛው ክፍለ-ዘመን ልዩ ሆኖ የሚታይበት አንድ ቁም ነገር አለ፡፡ በቀደሙት ክፍለ-ዘመናት አገሪቱን ሲያምሱ የቆዩ የፖለቲካና የጦር ግጭቶች መነሻቸው በአብዛኛው በዚያው ተንሰራፍቶ በነበረ ሥርዓት ክልል ውስጥ በመሪዎች መኻከል የሚቀሰቀሱ “የይገባኛል” ጥያቄዎች እንደ ነበሩ እናያለን፡፡ በሃኛው ክፍለ ዘመን እርግጥ በውስጥ በርካታ የስልጣን ግጭቶች ነበሩ፡፡ ከውጭ ወረራም አንፃር ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩን ኅልውና ለመንከባከብና ክብሩን ላለማስደፈር ከባድ የሕይዎትና የደም መሰዋእትነት የጠየቁ ትግሎች አካሂዷል፡፡ በፋሽሽት ጣሊያን ወረራ ሳቢያ እንኳ አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን እንደተሰው ታሪክ የመዘገበው ሐቅ ነው፡፡ ይኸም ሆኖ ሃያኛውን ክፈለ-ዘመን ካለፉት ሁሉ ልዩ የሚያደርገው ገና ከጧቱ በሥልጣን ይገባኛል ጥያቄ ሳይወሰኑ በአጠቃላይ ለኅብረተሰቡ ፍትኅን፥ ዴሞክራሲን፥ ዘመናዊ “ሥልጣኔን” የመሳሰሉ እሴቶችን አንግበው የተነሱ አዳዲስ ኃይሎች ብቅ ብቅ ማለት መጀመራቸው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የክፍለ-ዘመኑ ግጭቶች በአንድ በኩል ሰፊና አገራዊ አጀንዳ አንግበው ለበጎ ለውጥ በቆሙና በሌላ በኩል ደግሞ ይኸን የለውጥ አሳብ ለመፃረር በሚሞክሩ ኃይሎች መኻከል የተካሄዱ ግጭቶች ገፅታም እንደነበራቸው እናያለን፡፡

በክፍለ-ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከነዚህ አዲስ ራዕይ ጨብጠው ከተነሱ አዳዲስ ኃይሎች መካከል ከወቅቱ ምሁራን አንዱ የሆኑት አፈወርቅ ገብረየሱስ “ የአገራችን ገበሬ የልፋቱን ፍሬ ለወታደር ቀለብ እየተባለ የሚቀማበት፥ ተጨንቆ ተንከባክቦ ያረባውና ያሳደገው ፈረስና በቅሎ በባለሥልጣናት እየተመረጡ የሚወረሱበት” ግፈኛ ሥርዓት እስካልተወገደ ድረስ እሱም ተግቶ ለመሥራት የሚገፋፋው ነገር እንደሌለና አገሪቱም እንደ ቀረው ዓለም የመሰልጠን ዕድል እንደማየኖራት እየጻፉ ለለውጥ ይታገሉ ነበር፡፡ ከእሳቸው ይልቅ ደግሞ በተለይ በካህናቱ አካባቢ የተንፀባረቁ አንዳንድ ኋላ-ቀር አስተሳሰቦች ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ያሰሙ የነበሩት ምሁሩ ነጋድራስ ገብረ ኅይወት ባይከዳኝ በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ የሰፈነውን ፀረ-ሥልጣኔ አስተሳሰብ አምርረው እያወገዙ ከዚህ ይልቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሌሎቹ ጥንታዊ አገሮች ማለትም እንደ ጃፓንና ቻይና “ከእንቅልፉ እንዲነቃ” ይወተውቱ እንደነበረ ይታወቃል፡፡

አምሣ ዓመታት ተሻግረን በአገራችን መጀመሪያ ጎልቶ የታየው የታኅሣሡ ፲፱፻፶፫ ዓ/ም የለውጥ ሙከራ ከሽፎ መሪዎቹ ቤተ-መንግሥቱን ለቀው ከመሄዳቸው በፊት ባደረጉት የመጨረሻና የመሰነባበቻ ስብሰባ ንቅናቄውን ከመሩት መኻከል ወጣቱ ምሁር ገርማሜ ነዋይ ይኸንኑ የግፍና የኋላ ቀርነት ምሬት ባንፀባረቀ ንግግሩ አገራችን ከ“ቻይናና ከጃፓን ” ብቻ ሳይሆን በቅኝ ከተያዙ አፍሪካ አገሮች አንፃር እንኳን ያለችበትን አሳፋሪ ሁኔታ ሲጠቁም ፥

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

“ኢትዮጵያ ነፃ አገር ነች ብትባልም በቅኝ ግዛት ከሚገኙትና ትላንት ነፃ ከወጡት አገሮች አንፃር ለሚመለከታት የታሪክ ሰው በንጉሡ-ነገሥቱ ዘውዳዊ ሥርዓት የሕዝቡ አፍ ታፍኖ፥ ዓይኑ ተጋርዶ፥ የአገሪቱ ሃብትም የንጉሡ የግል ግምጃ ቤት ማዳበሪያ ሆኖ፥ የአገሪቱ ሕዝብ በድንቁርና ታስሮ፥ የአገሪቱ ሀብት የተቀራረበ ክፍፍል እንኳን ሳይደረግለት ሕዝቡ ለእርዛትና ለረሃብ የተዳረገ ኋላ-ቀር ከሚባሉት አገሮች መካከል መጨረሻ ሆና እንድትገኝ አድርጓታል፡፡”

“ከዚህ በመነሳት አገሪቱን ስንመለከት የጥቂት ምርጥ ቤተሰቦች መንደላቀቂያ ሆና ከምናይ ከእነዚህ ተባዮች አገዛዝ እጅ አውጥቶ እኩልነት፥ ነፃነትና ፍትኅ የገነነባት አገር ለማድረግ ለእድገትና ለብልፅግና እንድትበቃ ብንመኝም ለግል ጥቅም በተስገበገቡ ጥቂት ግለሰቦች ዓላማችን ለጊዜው ከግቡ ባይደርስም ይኸ ትውልድ ከመንግሥቱ አስተዳደር ቁንጮ ላይ ተቀምጦ የአገሪቱን እድገት ወደ ኋላ የሚጎትተውን አካል ከአገሪቱ የአመራር ሥልጣን የግድ ማስወገድ ይኖርበታል፡፡” የሚል ቃል ከተናገረ በኋላ በሌላው የንቅናቄው መሪ በነበረው በሌተና ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ አሳሳቢነት የመጨረሻ ቃላቸውንና በዓላማቸው ትክክለኛነትና ሕዝባዊነት የነበራቸውን እምነት ለታሪክ ለማስቀረት በቤተ-መንግሥቱ የክብር መዝገብ ላይ “ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለምንለትን ፈር ተክትሎ ዓላማውን ከግብ እንደሚያደርሰው እናምናለን፡፡” በሚል አረፍተ-ነገር ላይ ፊርማቸውን አስቀምጠው ቤተ-መንግሥቱን ለቀው እንደወጡ በንቅናቄው ተሳታፊ ከነበሩት ውስጥ ሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዓባይ በቅርቡ ለንባብ ባበቁት መጽሐፋቸው ጠቅሰዋል፡፡

ከዚያ ወዲህ የሆነው ሁሉ የቅርብ ትዝታ ነው፡፡ ለአገርና ለወገን ሲባል ታኅሣሡን በተከተሉት ዓመታት ስመ ጥሩው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ፥ ከዚያም የየካቲት ፷፮ አብዮታዊ ማዕበል፥ ከዚያም ታላቁና ታሪካዊው የግንቦት ፺፯ ንቅናቄ የአገራችን ዴሞክራቶች “ ለውጥ” ብለው ለሕዝብ ሲሉ ድምፃቸውን ባነሱ ቁጥር ያነገቧቸው የነፃነት፥ የፍትኅ፥ የዴሞክራሲ፥ የአገር ክብርና ብሔራዊ ነፃነት፥ የሕዝብ ወንድማማችነት የመሳሰሉትን ክቡር ዓላማዎች ያነገቡ እጅግ ከባድና ብዙ መስዋእትነት የጠየቁ ተጋድሎዎች ተካሂደዋል፡፡

ዛሬ እነሆ ክፍለ-ዘመኑም ከሁለተኛው አልፍ ዘመን ጋር ተገባዷል፡፡ ከመቶ ዓመታትም ሆነ ከአምሣ ዓመታት በፊት እነዚህና ሌሎች አገር-ወዳድ ምሁራን ከአለሙላትና ከታገሉላት የፍትኅና የዴሞክራሲ እርምጃ አሴቶች አንፃር የት ደርሰናል?

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) በተደጋጋሚ “ ዘግናኝና አሳፋሪ” ብሎ ስለፈረጀውና ዛሬ ስላለንበት ብቻ ሳይሆን አገራችንን ሊጠብቃት ስለሚችለው “ ዙሪያ-ገጠም ቀውስ” ለግንቦት ፺፯ ምርጫ ባወጣው አማራጭ ሰነድ ላይ ሲያትት ፥

“እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች አገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ አይታም ሰምታም በማታውቀው ሁኔታ ኅልውናዋንና የሕዝባችንን ሰላምና ደኅንነት የሚፈታተኑ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የማኅበራዊ፥ የአካባቢ ውድመትና ሌሎች ከባድ ቀውሶች ውስጥ መሆኗን በመገንዘብ፥
“ እነዚህ ቀውሶች ለዘመናት እየተጠራቀሙ የመጡ መሆናቸው የማይካድ ቢሆንም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት አንዳንዴም በቸልተኛነት ሌላ ጊዜ ደግሞ ሆን ብሎ በሚከተላቸው የተሳሳቱ ፖሊሲዎች የተነሳ አስደንጋጭ በሆነና ከዕለት ዕለት መመለሻ በሌለው ሁኔታ እየከፉና እየተባባሱ በመሄድ ላይ መሆናቸውን በማጤን፥

“እነዚህን ቀውሶች ለመቋቋምና አጥፊውን ሂደት ለመቀልበስ የሚቻለው በሉዓላዊት አገሩ ሉዓላዊ የሆነ ሕዝብ መክሮና ዘክሮ መፍትኄ ለመሻት የሚችልበት ዴሞክራሲያዊ መድረክ ሲመቻችለት ብቻ በመሆኑ፥

“ዛሬ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ተቀዳሚ ተግባር በጋራ ሰለማዊና ሕዝባዊ ትግል ይኸን መድረክ የነፈገውን መንግሥትና የአገዛዝ ሥርዓት አስወግዶ በሱ ቦታ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ክልል ውስጥ ጥረቱን የሚያግዝና የሚያስተባብር በሕዝብ ፊት ተጠያቂ የሆነ መንግሥት መመሥረት መሆኑን በመገንዘብ …” እያለ ከክፍለ-ዘመን የበጎ ለውጥ ትግልና መስዋዕትነትም በኋላ አገራችን ዛሬ አፍሪቃን ጨምሮ መላው ዓለምን በማላበስ ላይ ካሉት የዴሞክራሲና የፍትኅ እሴቶች ምንኛ ወደ ኋላ እንደምትገኝ ያለውን ግንዛቤ በምሬት አስቀምጧል፡፡

ይኽ የተገለፀው እውነታ ዛሬ ከፊታችን ከተደቀኑት ችግሮች አንፃር ብቻ አይደለም፡፡ መልእክቱ አገራችን በዚህ ይዞታ ከቀጠለች ኅልውናዋን ሳይቀር ሊፈታተኑ የሚችሉ ቀውሶች "በየ-ዕለቱ መመለሻ ወደሌለው ደረጃ" እየደረሱ እንደሆኑም በማስጠንቀቂያም መልክ የተሰነዘረ መልእክት ነበር፡፡ አለመታደል ሆኖ እነዚህ መስመሮች ከተጻፉ ወዲህ በተለይ ከግንቦት ሕዘባዊ እንቅስቃሴ መቀልበስ በኋላ ያለው የአገራችን ሁኔታ የዚህን መልእክት ወቅታዊነትና የሚጠበቅብን የአገር ማዳን ተልእኮ ከባድነት ኅሊና ላለው ማንም ዜጋ ያረጋግጥለታል፡፡

ከዚህ ስንነሳ ለቀጣዩ እልፈ-ዓመትም እንኳ ባይሆን "ለቀጣዩ ክፍለ-ዘመን ያላችሁ ራዕይ ምንድን ይሆናል?" ተብሎ ለሚጠይቀን ሁሉ ለእኛ በኢዴኃኅ ዙሪያ ተሰብስበን ለዚች ኩሩ አገራችንና ለዚህ ሰማዕት ሕዘባችን የምንታገልና የምንወደቅ አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች መልሳችን አጭር ይሆናል፡፡ አንደኛ ራዕይ አለን፤ ሁለተኛ ስጋት አለን፤ ሦስተኛ ምኞት አለን፡፡

ራዕያችን ምንም አዲስ ነገር የለውም፡፡ በዚህ ለበጎ ለውጥ በተደረገ ተጋድሎ በሰማዕታት በተትረፈረፈ ክፍለ-ዘመን ለአገር ለወገን ቆመናል እያሉ የታገሉና በሚሊዮን እየተቆጠሩ የተሰዉ ዜጎች ካንፀባረቁትና ዛሬም በፀረ-ሕዝብና አሸባሪ ሥርዓት ውስጥ ወድቀው የሚገኙ ሚሊዮኖች ከሚያልሙት የተለየ ምንም ራዕይ የለንም፡፡

በዓለም-አቀፍ ደረጃ የሄድን እንደሆነ ነባሩ ለዚች አገራችን ክብርና ኅልውና፥ ነባሩ ይቺ አገራችን በዓለም ሕዝቦች መድረክ አኩሪ ታሪኳ፥ አስተዋይና ታታሪ ሕዝቧ፥ ይኽ ነው የማይባል ተፈጥሯዊ ሀብቷ፥ የሚሰጧትን የክብር ቦታ ተመልሳ እንትይዝ የሚል የአገር ክብርና የወገን ኩራት ራዕይ ነው፡፡

በውስጥ የሄድን እንደሆነም ያው ነባሩ ይቺ አገራችን ፍትህና ዴሞክራሲ ሰፍነውባት፥ በብሔር/ብሔረሰቦቿ ስብጥር አሸብርቃና በሕዝቧ የትብብርና የወንድማማችነት መንፈስ ከብረት የጠነከረ አንድነት መሥርታ፥ ሰላም ወርዶ ከእንግዲህ ሚሊዮኖች ከረሃብና ከእርዛት ተላቀው መጭውን ጊዜ በብሩህ ተስፋና በሙሉ ልብ እየተመለከቱ አዲስ የተደላደለ ኑሮ ይገንቡ የሚል የብሩህ ተሰፋ ራዕይ አለን፡፡ ለዚህ ሁሉ እውንነት ደግሞ በተገባደደው ክፍለ-ዘመን እየተጠናወተን የኛንም ትግል የአቀበት ጉዞ አድርጎ የሕዝባችንንም የሰቀቆቃ ዘመን ካራዘመው የመከፋፈል አባዜ ተላቀን ለዚች አገር በጎ የምንመኝ ኃይሎች ሁሉ በአዲስ ክፍለ-ዘመን በአዲስ መንፈስና በአንድነት እንድንነሳ እንመኛለን፡፡

ዛሬ አገራችን ባለችበት "በታሪኳ አይታም ሰምታም በማታውቀው" የቀውስ ሁኔታ ደግሞ ብሩህ ራዕይን በማስተጋባት ብቻ መወሰን አይቻልም፡፡ ይኽን ድልና ሽንፈት የተፈራረቁበት "አሻሚ" ክፍለ-ዘመን ወደ ኋላ ትተን ለዚች ዘላለማዊት ለተባለች ኢትዮጵያ አሁንም እንደ ጀግኖች አባቶቻችን ቆመናል ካልን በአገራችን ሰማይ ላይ የየካቲት ቅልበሳ የጀመረው የአንድነቷና የኅልውናዋ መፍረክረክ አደጋ በግንቦት ቅልበሳም ሳቢያ እያንዣበበባት እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ከዚህ ተነስተን ከየካቲት ቅልበሳ ባሻገር የግንቦትም ቅልበሳ የካቲት የጀመረውን አፍራሽ ሂደት ቀጥሎ ለአገራችን አንድነትና ለሕዝባችን ሰላም አደገኛ ሁኔታ ይፈጥራል የሚል ስጋትም አለን፡፡ ይኽ ስጋታችን ከፀረ-ሕዝብና ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች "ኃያልነት" የሚፈልቅ ስጋት አይደለም፡፡ በታሪኩ እየወደቀ መነሳት የለመደበት ታጋይ ሕዝባችን በአንድነት በቆመ ቁጥር እንኳን እነዚህ ጥቂቶች ቀርቶ በመሣሪያና በሀብት "ኃያላን" የሚባሉ የኦቶማን ቱርክ ወራሪዎችንም ሆነ የአውሮጳ ቅኝ ገዥ ጠላቶችን በጦር ሜዳ እያሳፈረ ክብሩን ያስጠበቀና ማንነቱን ያረጋገጠ ሕዝብ ነው፡፡ የኛ ስጋት የሚመነጨው ከሕዝባችን ብቃት ማነስ ወይም ቁርጠኝነት ማጣት ሳይሆን ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ እንደሆነ በአንዳንድ ወገኖች ካለውና ከሚታየው የግንዛቤ እጥረትና የመተባበር ጉድለት ነው፡፡

ትልቁ ስጋታችን ዛሬ በአገር-ወዳዶችና በዴሞክራቶች ጎራ ባለው የመበታተን ሁኔታ በመንግሥት ደረጃ ባለቤት ያጣች አገራችን በአገራዊ አማራጭ ደረጃም ባለቤት ያጣች አገር

ልትሆን ትችላለች የሚል ስጋት ነው። ትልቁ ስጋታችን ይኸ ሁሉ ግንዛቤ እያለም "ብሩን ተስፋ" ላይ በማተኮር በያዝ-ለቀቅ ከሚካሄድ ትግል ይልቅ ዛሬ የሚያስፈልገን አገራችን ከምትገኝበትና እየከፋ ሊሄድ ከሚችል ከፍተኛ አደጋ ለማዳን የተያያዝነው " የአልሞት ባይ ተጋዳይ " ትንንቅ እንደሆነ ተገንዝበን ይኸ ስሜት ብቻ ሊሰጥ በሚችለው ፍጹም ቆራጥነትና ፍጥነት ለመታገል ስንነሳ አለመታየታችን ነው።

ይኸንን ሁሉ ስጋት አሸንፈን የሁላችንም የሆነውን ነባሩንና ጊዜ የማይሽረውን ራዕያችንን እውን ለማድረግ በዚህ አዲስ የሃያ-አንደኛው ክፍለ-ዘመን እየነጋ ባለበት ወቅት የምናስተጋባው አገራዊ ጥሪ አንድና አንድ ብቻ ነው። በተገባደደው ክፍለ-ዘመን ከባድ መስዋዕትነት ለተገበረለት ኢትዮጵያዊነት ህልማችን "ዛሬ ትብብር፥ ነገ ውድድር" ብለን በአንድነትና በአዲስ መንፈስ እንነሳ!! ዛሬ አገራችን ባለችበት አስከፊ ሁኔታ ኢዴኃኅ ከዚህ የተለየ ምንም ሌላ ራዕይም፥ ህልምም፥ ምንም ሌላ ጥሪና ምንም ሌላ ምኞት የለውም። ሊኖረውም አይችልም።

የቂም-በቀልና የአምባ-ገነኖች አዙሪትን በተባበረ የጋራ ትግል በማስወገድ አገራችንንና ሕዝባችንን ከበሽታና ከችጋር አላቀን ዘለቄታዊ የተደላደለ ሰላምና የፍትኃዊ ሥርዓት ባለቤት ለማድረግ ሁሉም በቁርጠኝነት ይነሣ!

አዲሱ ዓመት የሰላም፥ የፍቅር፥ የአንድነት፥ የትብብር፥ የወንድማማችነት፥ የሕግ የበላይነት፥ የፍትኅ፥ የርትዕና የጋራ ድል ዓመት እንዲሆን ከልብ እንመኛለን!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)